የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ መንግስት
የከንቲባው ስራ አስፈጻሚ ጽህፈት ቤት

የተጎጂዎች አገልግሎትና የፍትህ ስርዓት ገንዘብ ድጋፍ ጽ/ቤት

# የ2016 የበጀት የማመልከቻዎች መጠየቂያ (RFA): የግል የደህንነት ካሜራ ማበረታቻ ፕሮግራም

## <u>ወሳኝ ማስታወቂያ</u>

**የኤሌክትሮኒክ የድጎማዎች አስተዳደር ስርዓት (eGMS) ZoomGrants™ በኩል የተደረገ ማመልከቻ**

**ማመልከቻውን ለማግኘት የሚከተለውን ይንኩ http://www.ovsjg.dc.gov**

## 1. አጠቃላይ መረጃ

***መግቢያ***

የከንቲባው የስራ አስፈጻሚ መስሪያ ቤት፣ የተጎጂዎች አገልግሎትና የፍትህ ስርዓት ገንዘብ ድገፍ ጽ/ቤት (The Executive Office of the Mayor, Office of Victim Services and Justice Grants (OVSJG) የወንጀል፣ የህዝብ ደህንነት እና የወንጀል ፍትህ ስርዓት ችግሮችን በሚመለከት የሚሰሩ ከእዚሁ አካባቢ የሚነሱ ስራዎችን በገንዘብ ይደግፋል። OVSJG በግል የደህንነት ካሜራ ማበረታቻ ፕሮግራም መሰረት የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ ማመልከቻዎችን እየተቀበለ እንደሆነ ሲያበስር በደስታ ነው።

ይህ ፕሮግራም የንብረት ባለቤቶች፣ የንግድ ባለቤቶች፣ እንዲሁም ለትርፍ ያልተቋቋሙና የሃይማኖት ተቋማት ወንጀል እንዳይስፋፋና የህግ ማስከበር አካላትን እንዲያግዝ ለማስቻል የደህንነት ካሜራ እንዲገጥሙ ማበረታቻን ይፈጥራል። ፕሮግራሙ የደህንነት ካሜራዎችን ለመግዛትና ለመግጠም ያወጡትን ገንዘብ በመመለስ ድጋፍ ያደርጋል።

**አስተዳደራዊ መስፈርቶች**

***የማመልከቻ መስፈርቶች***

አመልካቾች ለአንድ ካሜራ እስከ $200 እንዲሁም ለመኖሪያ ቦታ በአጠቃላይ እስከ $500 እንዲሁም ከመኖሪያ ለተለየ አገልግሎት ለሚውል ንብረት እስከ $750 ድረስ ያወጡት ወጪ እንዲመለስላቸው ማመልከት ይችላሉ። ካሜራዎቹ የተገዙት ከሴፕቴምበር 22 ቀን 2015 በኋላና ለፕሮግራሙ የተመደበው ገንዘብ ከማለቁ በፊት የተገዙና የተገጠሙ መሆን አለባቸው። ካሜራዎቹ በተጨማሪም በሜትሮፖሊታን ፖሊስ ዲፓርትመንት መመዝገብ አለባቸው። ተመላሽ የሚደረገው የገንዘብ መጠን የካሜራ ሲስተሙ ከተገዛበት ዋጋ መብለጥ የለበትም። በአንድ ንብረት ላይ ተመላሽ ክፍያ መጠየቅ የሚቻለው ለአንድ የካሜራ ሲስተም ብቻ ነው። የደህንነት ካሜራ ስርዓቱ የሚገጠመው በህንጻው የውጪ ክፍል ላይ ነው።

***ለፕሮግራሙ የተመደበው ገንዘብ መኖር***

በዚህ ፕሮግራም ውስጥ የተመደበውን ገንዘብ ማግኘት የሚቻለው **ከፌብርዋሪ 2 ቀን 2016** ጀምሮ የተመደበው ገንዘብ በሙሉ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ነው። ሁሉም ተመላሽ የሚደረጉ ወጪዎች በዚህ የጊዜ ክልል ውስጥ የወጡ መሆን አለባቸው። ከፕሮጀክቱ መጀመር በፊት እንዲሁም ፕሮግራሙ ካበቃ በኋላ የወጡ ወጪዎች እንዲመለሱ መጠየቅ አይፈቀድም።

በተጨማሪም የተጎጂዎች አገልግሎትና የፍትህ የገንዘብ ድጋፎች ጽ/ቤት ያለምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ በዚህ የማመልከቻ መጠየቂያ ውስጥ የተጠቀሰውን ፕሮግራም የመሰረዝ፣ ሁሉንም ማመልከቻዎች የመሰረዝ፣ የተመደበውን አጠቃላይ በጀት የማስተካከል ወይም ይህንን የማመልከቻ መጠየቂያ በሙሉም ይሁን በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

ለፕሮግራሙ የተመደበው የገንዘብ መጠን ከዲስትሪክቱ የሚመደበው በጀት ላይ የተመሰረተ ነው።

***በቅድሚያ ግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ነገሮች***

የተጎጂዎች አገልግሎትና የፍትህ የገንዘብ ድጋፎች ጽ/ቤት በሚከተሉት የፖሊስ አገልግሎት ክልሎች (Police Service Areas (PSA)) ስር ላሉ ንብረቶች፣ ንግዶች እና ሃይማኖታዊ ተቋማት ቅድሚያ ይሰጣል:

- PSA 103
- PSA 104
- PSA 105
- PSA 106
- PSA 107
- PSA 108
- PSA 202
- PSA 207
- PSA 208
- PSA 302
- PSA 303
- PSA 305
- PSA 307
- PSA 308
- PSA 402
- PSA 403
- PSA 404
- PSA 405
- PSA 406
- PSA 407
- PSA409
- በአምስተኛው ዲስትሪክት ውስጥ ላሉ ሁሉም PSAs
- PSA 601
- PSA 602
- PSA 603
- PSA 604
- PSA 607
- PSA 608
- በሰባተኛው የፖሊስ ዲስትሪክት ውስጥ ላሉ ሁሉም PSAs

የ PSA ክልሎች በሚከተለው አድራሻ ማግኘት ይቻላል፡ http://mpdc.dc.gov/page/police-districts-and-police-service-areas ። አመልካቾች ንብረታቸው የሚገኝበትን PSA በሚከተለው አድራሻ ማግኘት ይችላሉ: http://geospatial.dcgis.dc.gov/PSAFinder ።

***የማመልከቻ መረጃ***
ኤሌክትሮኒክ ማመልከቻው ለፕሮግራሙ የተመደበው ገንዘብ ጥቅም ላይ ውሎ ከማለቁ በፊት ለተጎጂዎች አገልግሎትና የፍትህ የገንዘብ ድጋፎች ጽ/ቤት መድረስ አለበት። ማመልከቻዎችን ከ www.ovsjg.dc.gov ማግኘት ይቻላል። በእጅ የተጻፈ ማመልከቻ ተቀባይነት የለውም። እባክዎ ማመልከቻውን ከማብቂያው ቀን በፊት በ ZoomGrants™ በኩል ገቢ መደረጉን ማረጋገጥ የአመልካቹ ሃላፊነት መሆኑን ይገንዘቡ።

ከተጠቀሰው ጊዜ በኋላ የሚገባ ማንኛውም ማመልከቻ ተቀባይነት የሌለው ሲሆን የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት አይታይም።

***የገንዘብ ድጋፍን ማሳወቅ***
የተጎጂዎች አገልግሎትና የፍትህ የገንዘብ ድጋፎች ጽ/ቤት ለሁሉም አመልካቾች ጥያቄያቸውን በሚመለከት ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ10 ቀናት ውስጥ የመጨረሻውን የገብዘብ መመለስ ውሳኔ ያሳውቃል። ክፍያዎች ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ45 የስራ ቀናት ውስጥ ይፈጸማሉ። የገንዘብ ድጋፍ ለሚደረግላቸው አመልካቾች ይህ ማሳወቂያ ተመላሽ የሚደረግላቸውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ ሲሆን ካመለከቱት መጠን የተቀነሰ የገንዘብ መጠን ካለ ይህንኑ ያመለክታል።

***ቅሬታ የማቅረብ ሂደት***
ማመልከቻቸው ተቀባይነት ያላገኘ አመልካቾች የገንዘብ ድጋፉ ያልተደረገበትን ውሳኔ ማብራሪያ እንዲሰጣቸው በጽሁፍ በሚከተለው አድራሻ መጠየቅ ይችላሉ:
Office of Victim Services and Justice Grants
ATTN: Application Inquiry – Private Security Camera Incentive Program
441 4th Street, NW, Suite 727N
Washington, DC 20001
ኢሜይል: security.cameras@dc.gov

***የክፍያዎች አፈጻጸም***
የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ መንግስት ክፍያዎችን በዚህ የማመልከቻ መጠየቂያ ላይ በሚመሰረተው ክፍያዎችን ተመላሽ የማድረግ ስምምነት መሰረት ይፈጽማል። የመጨረሻ ክፍያው ከመደረጉ ከማንኛውም ጊዜ ወይም ጊዜያት በፊትና ከዚያ በኋላ ባሉት ሶስት (3) አመታት ውስጥ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ መንግስት ማመልከቻውንና በማመልከቻው ውስጥ የተጻፉትን ነገሮች ኦዲት ሊያደርግ ይችላል።

OVSJG ለዚህ የማመልከቻ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ላወጡት ማንኛውም የማመልከቻ ወጪ ሃላፊነቱን አይወስድም። አመልካቾች ማመልከቻውን ለማዘጋጀት የሚወጡ ማናቸውም ወጪዎች አመልካቹ ሙሉ ሃላፊነት እንደሆነ ይስማማሉ።

OVSJG በማመልከቻው ላይ የተጠቀሱትን ነገሮች ለማረጋገጥ የገንዘብ ድጋፉን ከማድረጉ በፊት በቦታው በመገኘት ሊጎበኝ ይችላል።

በማመልከቻ መጠየቂያውና በማንኛውም የፌዴራል ወይም የዲስትሪክት ህግ ወይም ደንብ ላይ ማንኛውም አይነት ግጭት ቢኖር ወይም ማንኛውም አይነት አሻ ነገር ቢኖር የህጉ ወይም ደንቡ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ የሚሆኑ ሲሆን አመልካቹ እነዚህ ህጎች እንደተከበሩ የማረጋገጥ ግዴታ አለበት።

***የግምገማ ሂደት እና የገንዘብ ድጋፍ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ***
አመልካቹ የብቁነት መስፈርቶችን በጠቅላላ እንደሚያሟላ፣ አመልካቹ ቅድሚያ የሚሰጠው አመልካችነትን መስፈርት እንደሚያሟላ፣ እንዲሁም ሁሉንም የሚያስፈልጉ ሰነዶች እንዳስገባ ለማረጋገጥ ይታያሉ። አንድ ጊዜ ከላይ የተጠቀሱት መስፈርቶች እንደተሟሉ ከተረጋገጠ በኋላ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ OVSJG በቦታው ተገኝቶ ቦታውን ለማየት ከአመልካቹ ጋር ይነጋገራል።

የደህንነት ካሜራው መገጠሙ ለመጨረሻ ጊዜ ከተረጋገጠ በኋላ የገንዘብ ድጋፉ ይህ ፕሮግራም ተገዢ በሆነባቸው የዲስትሪክት ህጎችና ደንቦች መሰረት ይደረጋል።

## II. የማመልከቻ መመሪያዎች

***የአመልካች መግለጫ***

እያንዳንዱ አመልካች ሁሉንም በማመልከቻ ውስጥ እንዲካተት የተጠየቀውንና ስልጣን ባለው አካል የተረጋገጠ መረጃን በሙሉ ማካተት አለበት። ስልጣን ያለው አካል ማለት አመልካቹን በመወከል የመፈረም ስልጣን ያለው ሰው ማለት ነው።

አመልካቹ **የንብረት ባለቤት የሆነ ግለሰብ** ከሆነ ስልጣን ያለው አካል የንብረቱ ህጋዊ ባለቤት መሆን አለበት።

አመልካቹ ***የንግድ ባለቤት፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ*** ወይም ***የሃይማኖት ተቋም*** ከሆነ ስልጣን ያለው አካል ማለት በንግድ ወይም በሃይማኖት ተቋሙ ስም ለመፈረም ህጋዊ ስልጣን ያለው ሰው መሆን አለበት።

ግለሰቡ፣ የንግድ ባለቤቱ ወይም የሃይማኖት ተቋሚ የግል የደህንነት ካሜራው የሚገጠምበት ንብረት ህጋዊ ባለቤት ከሆነ (ለምሳሌ **የንብረቱ ተከራይ ከሆኑ**) ማመልከቻውን የሚያስገባው ግለሰብ፣ የንግድ ድርጅት ወይም የሃይማኖት ተቋም የግል የደህንነት ካሜራው ከሚገጠምበት ንብረት ባለቤት ከሆነው ሰው የንብረቱ ባለቤት የግል የደህንነት ካሜራው እንዲገጠም መፍቀዱን የሚገልጽ ደብዳቤ አያይዞ ማስገባት አለበት።

### *የደህንነት ካሜራ ግዢና ደረሰኝን ማረጋገጥ*
እያንዳንዱ አመልካች የደህነነት ካሜራ መግዛቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለበት። መግዛቱን ከሚያረጋግጡ ማስረጃዎች መካከል የሽያጭ ደረሰኝ፣ የመላኪያ ደረሰኝ እና/ወይም የመረከቢያ ደረሰኝ ይገኙበታል። ለዚህ ፕሮግራም ብቁ የሚሆኑት ከሴፕቴምበር 22 ቀን 2015 በኋላ የተገዙ የደህንነት ካሜራዎች ብቻ ናቸው።

### *የደህንነት ካሜራ መገጠም ማረጋገጫ*
የደህንነት ካሜራ ሲሰተም ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ ለማመልከት ብቁ እንዲሆን አስቀድሞ እንደተገጠመ መረጋገጥ አለበት። አመልካቹ መገጠሙን በሚከተሉት መንገዶች ማረጋገጥ ይችላል: 1) የደህንነት ካሜራው የተገጠመው የደህንነት ስርዓቶችን ለመግጠም የሚያስችል መሰረታዊ የንግድ ፈቃድ ባለው የንግድ ድርጅት ከሆነ የንግድ ድርጅቱ በንበረቱ ላይ የተደረገው የካሜራ ሲስተም መገጠሙን በፎቶግራፍ ማስረጃ በማስደገፍ ማረጋገጥ አለበት፤ ወይም 2) የደህንነት ካሜራው የተገጠመው በንብረቱ ባለቤት፣ በንግድ ድርጅቱ ባለቤት ወይም መሰረታዊ የንግድ ፈቃድ በሌለው በማንኛውም ሰው ከሆነ አመልካቹ ጽ/ቤቱ በቦታው በመገኘት የደህንነት ካሜራው መገጠሙን እንዲያረጋግጥ ማሳወቅ አለበት።

### *በሜትሮፖሊታን ፖሊስ መምሪያ የምዝገባ ማረጋገጫ*
እያንዳንዱ አመልካች የደህንነት ካሜራው በ http://mpdc.dc.gov/securitycameraregistration በሚደረገው የሜትሮፖሊታን ፖሊስ መምሪያ መመዝገቡን መረጋገጫ ማስገባት አለበት።

አመልካቹ የደህንነት ካሜራው መመዝገቡን የሚያረጋግጥ ኢሜይል ከሜትሮፖሊታን ፖሊስ መምሪያ ይደርሰዋል። የደህንነት ካሜራዎቹ ማመልከቻው ገቢ ከሚደረግበት ጊዜ በፊት በሜትሮፖሎታን ፖሊስ መምሪያ መመዝገብ አለባቸው።

### *የንብረት ባለቤቱ ፈቃዶች (ተፈጻሚ ከሆነ)*
ከላይ እንደተጠቀሰው አመልካቹ የደህንነት ካሜራው የሚገጠምበት ንብረት ባለቤት ካልሆነ (ማለትም ተከራይ ከሆነ) አመልካቹ ከንብረቱ ባለቤት የተጻፈ ባለቤቱ ንብረቱ ላይ የደህንነት ካሜራ እንዲገጠም መፍቀዱን የሚገልጽ ደብዳቤ ማቅረብ አለበት። ማመልከቻ ለሚያስገቡ ለማናቸውም ተከራዮች ይህ ደብዳቤ ከማመልከቻው ጋር አብሮ መግባት አለበት።

## *ማመልከቻ ሊያካትታቸው የሚገቡ ነገሮች*

### *ማመልከቻ ውስጥ መካተት ያለባቸውን ነገሮች መከታተያ*
የሚከተለው መረጃ የዚህ የማመልከቻ መጠየቂያ የተሟላ ምላሽን የሚወክል ሲሆን ከማመልከቻ ማብቂያ ቀኑ በፊት ገቢ መደረግ አለበት:

- ☐ የአመክካች ማንነት መግለጫ
- ☐ የካሜራ ግዢ ደረሰኝ
- ☐ በሜትሮፖሊታን ፖሊስ መምሪያ መመዝገቡን የሚገልጽ ማረጋገጫ
- ☐ ከንብረቱ ባለቤት ፈቃድ መሰጠቱን የሚገልጽ መግለጫ (አስፈጊ ከሆነ)
- ☐ የመገጠም ማረጋገጫ